#የእናት ፍቅር

ክፍል - 4

.....ሳያት ተናዳለች ምን ሆነሽ ነው አልኳት ምንም አልሆንኩም አለች በጣም እንደተረበሸች ያስታውቃል ለማንኛውም ግን ብላ እየጮኸችብኝ ብቻ ቦርሳዋን ከፈተችና የሆነ ወረቀት ሰጠችኝ ምንድ ነው አልኳት ቤት ስትገቢ አንብቢው ብላ መልሴን ሳጠብቅ ጥላኝ ሄደች .....
የዚች ልጅን ነገር ሳስበው በጣም ግራ ተጋባሁ ወረቀቱን እስካየው ድረስ ቸኮልኩ በርግጥ ሲበዛ ለምንም ነገር ቦታ የላቸውም ከሆነ ሆነ ካልሆነ ገደል ይግባ የሚሉ ልጆች ናቸው ጓደኞቼ በብዛት ለምንም ነገር የማይጨነቁ ናቸው ለዛምይሆናል እኔ ችላተኛ የሆንኩት የመሰልኝ ከዛ ቀን ጀምሮ ሁሉምነገርእየሰለቸኝነው ፡፡ ከግዜ ወደ ግዜ እናቴም ህመሟ እየበረታባት መጣ እንደ ዛም ሆና እራሱ ግን ፀባዬ በቃ ምንም አለቀኝ አለ ሁሌም የለመዱትን
ባህሪ እርግፍ አድርጎ አንደቀላል ነገር መተው ይከብዳል የሚከብደኝ
ውስጤ ደግሞም ስፈጠር ጀምሮ እራሴን እስካውቅ ድረስ ተሰምቶይ የማላውቅ ልጅ አሁን ግን ልቤን ፍረሀት ፍረሀት ይለኛል እናቴ በዚህ መሀል ወደ ፀበል ልሂድ ነው ስላለችኝ መሰለኝ ምን እንደማደርግ ግራገብቶኛል ማታ ላይ ሜሪ የሰጠችኝን ወረቀት ሳየው በጣምተናደድኩ ምንም የተፃፈበት ነገር የለም ምን ማለት እንደፈለገች ምንም አልገባኝም ከሁለት ቀን በኋላ እናቴ ወደ ፀበል

☎ +251-991192111 @stefantekka
+251-920-59-46-52 ✉ @achirlebwold አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
E-Mail: stefantekka52@gmail.com Fax 251-11-11-11 Addis Ababa, Ethiopia

የእናት ፍቅር@chirlebwold

ሄደች እኔም በህይወቴ ለመጀመርያ ግዜ ባዶነት ተሰማኝ በቃ እናቴንምይሁን ከእኔ ርቃ አታውቅም አሁን ግን በቃ ህይወቴ ያለ እሷ ባዶ የሆነ ያህል ተሰማኝ እሷን የሰደብኩበትን ቀን ሳስብ ራሴን እረግማለሁ ስልኬን አጠፋፍቻለሁ ማንንም ማግኘት አልፈለኩም ሊዱም እቤት

ድረስ እየመጣች ታጫውተኛለች በጣም የገረመኝ ግን በችግራቸው ግዜ የደረስኩላቸው ሰዎች አብሪያቸው ውዬ ያደርኩላቸው ሰዎች ጭራሽ አላስታወሱኝም ፍቅረኛዬ ያልኩት አሌክስ እንኳን ረስቶኛል መሰለኝ.....

ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ሊዱ ቤት ልሄድ ስወጣ መንገድ ላይ አሌክስ አገኘኝ አንዴ አንቺ ምን ሆነሽ ነው የጠፋሽው ምናምን አለኝ መልስ ሳልሰጠው ይቀባጥር ጀመረ እቺደደብ የሆነች ጓደኛሽ ነገረችሽ አይደል አለ እንዳታምኛት ደግሞ እርግጠኛ ነኝ እውነቱ እንደሱ አይደለም እውነቱን እኔ እነግርሻለሁ አንዴ ስሚኝ አለ ምንም ነገር ሳልለው እንደዚ መቀበጣጠሩ እንድጠራጠረው አረገኝ ከዛም በጣም ደነገጥኩ የሆነ ነገር እንዳለ ገባኝ አሌክስ ድምፁን ከፍ አድርጎ እኔ ከሜሪ ጋር .....

#ይቀጥላል.....

☎ +251-991192111 @stefantekka
+251-920-59-46-52 ✉ @achirlebwold አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
E-Mail: stefantekka52@gmail.com Fax 251-11-11-11 Addis Ababa, Ethiopia